<u>የረቡዕ ሐምሌ 13 1997 ዓም( የጁላይ 20 2005)</u>

## <u>የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ</u>

## <u>በኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም ላይ የተመሠረተ የኅብረት ትግል አስፈላጊነትና ወቅታዊነት</u>

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ከመስቀለኛ መንገድ በደረሰበት ወቅት፥ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ አንገብጋቢ ሆኖ የተገኘው፥ በኢትዮጵያ ዘለቄታና ብሔራዊ ጥቅም ላይ <u>ብቻ</u> የተመሠረተ የሕብረት ትግል መሆኑ ሊያከራክር ከቶ አይችልም። በዚህ መርህ-ግብር ላይ የተገነባ ኅብረት፥ ምን ጊዜም ቢሆን ሊናወጥና ሊፈረካከስ አይችልም። እያንዳንዱ የተቃዋሚ ድርጅት፥ ይህንን መሠረታዊና አንገብጋቢ ብሔራዊ የትግል አንቀጽ መገንዘብ ብቻ ሳይሆን፥ በተግባር እንዲተረጉም ይጠበቅበታል። የፖለቲካ ድርጅቶች የሚታገሉት ያው ዞሮ ዞሮ ለሥልጣን መሆኑ ባይካድም፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብሔራዊ ጥቅምና ስትራተጂያዊ ራዕይ ካላገናዘበ ትግል የሚመጣ ሥልጣን ግን የትም አይደርስም። ምናልባት ጊዜያዊ ምኞትን ሊያረካ ይችል ይሆናል። የሕዝብን ድጋፍም ይሁን የትውልድን ምስጋና ግን ጭራሽ አያገኝም። ትግሉም፥ ፋይዳም ሆነ ዘለቄታ፥ መቅኖም ሆነ እርባና አይኖረውም። ለሀገሪቱ ችግሮች ዘለቂታ መፍትሄ አያመጣም። የሀገሪቱን ሉዓላዊነት፥የሕዝቡን አንድነት፥ ክብርና ጥቅም በዘለቄታ መልኩ ማስጠበቅ የሚቻለውም፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ በሀገሪቱ ዘላቂና መሠረታዊ ዓላማ ዙሪያ ተሰባስበው በኅብረት መታገል ሲጀምሩ ብቻ እንደሆነ መታወቅ አለበት። የኢትዮጵያን ሕዝብ ስትራተጂያዊ ጥቅም ወደጎን በመተውና ለጊዜያዊ የሥልጣን ጉጉት ርካታ ሲባል የሚወሰድ እርምጃ ሁሉ፥ እንደ ጧት ጤዛ ታይቶ ወዲያው እንደሚረግፍ አስቀድሞ መታወቅ ይኖርበታል።

የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ ዛሬ በዚህ መሠረታዊ፥ ብሔራዊ፥ ስትራተጂያዊና የዘለቂታ ጥቅም ላይ የተገነባ ኅብረት ፈጥረው በመታገል ላይ ናቸው ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማመን ተስኖታል። ለዚህም ይመስለናል ባለፈው ግንቦት ወር፥ ማንም ሳይቀሰቅሰው፥ ሳይመራው፥ ሳያደራጀውና ሳይጠራው፥ በራሱ አነሳሽነት ወጥቶ የአዲስ አበባን ከተማ ያጥለቀለቀ ሰላማዊና ሕዝባዊ ሰልፍ አድርጎ፥ የወያኔን ሥርዓት ከስር መሠረቱ ሊያናውጥ የበቃው። ይህ በራሱ በውስጡ የተነሳሳው ሕዝባዊ አመፅ፥ የኢትዮጵያን የፖለቲካ መልካምድር ብቻ ሳይሆን፥ የትግሉንም ይዘትና ዓይነት፥ አቅጣጫና ዓላማ በዘለቄታ መልኩ ለውጦታል ማለት ይቻላል። ይህንን ለማለት የሚቻለውም፥ በርካታ፥ አሳማኝና ተጨባጭ ክስተቶች በመፈጠራቸው ነው።

1. ከሁሉ መጀመሪያ ከእንግዲህ ወዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማንኛውም አምባገነን ሥርዓት በቀላሉ የማይገዛ መሆኑን ለዓለም አስመስክሯል ። ለወያኔ መሪዎችም ጠንካራ መልዕክት አስተላልፏል። ሰላማዊ ሰልፉንም

ያካሄደው በዘር፥ በቋንቋና በሃይማኖት ሳይከፋፈል ነበር። ይኸም የወያኔን የከፋፋይ ሴራ አክሽፎበታል።

2. የወያኔ መሪዎች የትዕቢት ፊኛቸው መተንፈሱ ብቻ ሳይሆን፥ ያልጠበቁት ዱብ-ዕዳ ስለመጣባቸው፥ ከድንፋታ ወደ መርበትበት በመለወጣቸው፥ በሰላማዊው ሕዝብ ላይ ጭፍጨፋ አካሄደዋል። ሴት ወንድ፥ ህፃን ሽማግሌ፥ ሳይለዩ በርካታ ንፁህን ዜጎችን ረሽነዋል፡ ከመቶ በላይ የሚቆጠሩትንም አቁስለዋል። ይህ እርምጃቸው ጥንካሬን ሳይሆን ድክመትን ብሎም ውድቀትን የሚያሳይ ነው። የዚህ ንፁሓን ደም ግን በከንቱ ፈስሶ የሚቀር አይሆንም። የጊዜ ጉዳይ ነው!!

3. የተቃዋሚ ድርጅቶችም፥ የሕዝቡ አመፅ ምን ያህል ከእነርሱ ልቆ፥ መንጥቆና አልፎ እንደሄደባቸው ለመረዳት ችለዋል። ለአለፉት ሦስት ወራት በኢትዮጵያ የሚካሄደው የሕዝቡ ሰላማዊ አመፅ፥ አሁንም የሚንከባከበው፥ የሚያግዘው፥ የሚመራውና የሚያስተባብረው ማንም በበቂ የጠነከረ ኃይል አለመኖሩ በግልፅ ታይቷል። ይህም ሃቅ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል አስቆጭቶታል፥ አስቆጥቶታል። አስከፍቶታልም።

4. በግንቦቱ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመለስን አገዛዝ በድምፁ ቢያስወግደውም፥ የሕዝብን ውሳኔ አልቀበልም በማለት የወያኔ መሪዎች አሁንም የአምባገነን አገዛዛቸውን ቀጥለዋል። የሕዝቡን ውሳኔ ለማስከበር አንዳችም የማስፈፀሚያ ኃይል የሌለው የተቃዋሚ ጎራ፥ ዛሬም እንደ ትላንቱ የጠነከረ ኅብረት ፈጥሮ የሕዝቡን ጥሪ ሊመልስ አልቻለም። ሕዝብና የተቃዋሚ ጎራ በአንድ ዓይነት የትግል አውድማ ውስጥ አይደሉም። ተመሳሳይ አቅጣጫ አልያዙም። ሕዝብ እየመራ ተቀዋሚ ድርጅቶች እየተመሩ ለመሆኑ ያገጠጠ ያፈጠጠ ሃቅ ሆኗል። ይህንን እንደ እንቆቆ የሚጎመዝዝ ሀቅ ተቀብለው፥ የኅብረት ትግላቸውን አጠንክረው የሕዝቡን ትግል መምራት ካልቻሉ፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች በታሪክና በትውልድ እንደሚጠየቁ ለአንድ አፍታም ቢሆን ሊረሱት አይገባቸውም።

5. የተቃዋሚ ድርጅቶች ይህንን መገንዘብ ሳይችሉ ቀርተውና የሕዝቡንም ትግል ክደውና አኮላሽተው ከመለስ ዜናዊ ጋር ቢደራደሩ፥ የሕዝብን ከበሬታና አመኔታ፥ ያገኛሉ ማለት ዘበት ነው። የሕዝብን ንቀት፥ ጥላቻና ተቃውሞ ያተረፈ ደግሞ ምን እንደሚመስል፥ ከመለስ ዜናዊ ዘረኛ ሥርዓት የመነጨው መንግሥት ምን እንደሆነ ማየቱ ብቻ ይበቃል።

6. ምዕራባውያን በኢትዮጵያ ላይ የነበራቸውን ፖሊሲ በመለወጥ ላይ እንደሚገኙ፥ ከሚያወጧቸው መግለጫዎችና ውሳኔዎች ለመረዳት ተችሏል። ቢሆንም፥ ተቃዋሚውንና የገዥውን ፖርቲ ለማቀራረብ የሞከሩት ጥረት እስካሁን ፋይዳ አላመጣም። ለዚህም ይመስላል

““*መቸነፉን ለመቀበል ያልተዘጋጀ መንግሥት፥ አቸንፎ ግን፥ሥልጣን ለመረከብ ያልተዘጋጀ የተቃዋሚ ክፍል*” እስከ ማለት የበቁት፡፡ ይህ የምዕራባውያኑ ግንዛቤ የወቅቱን የሀገራችንን ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ይመስለናል፡፡ እንዲያውም፥ የሀገሪቱን የወቅቱ የፖለቲካ መልከዓ-ምድር ላስተዋለው ዜጋ፥ ሦስት የፖሊቲካ ተዋናዮች እንደተፋጠጡ ይገነዘባል፡፡ እነርሱም፡-

ሀ) የመለስ ዜናዊን ፀረ ዴሞክራሲ አገዛዝ ተቃውሞና አሻፈረኝ! አልገዛም! ብሎ የወጣ የሕዝብ አመፅ አለ፡፡ ይህ ሕዝባዊና ሰላማዊ የትግል አመፅ ግን አለሁ ያለው መሪ የለውም፡፡

ለ) ማድረግ ያለበትን በጋራ ያልተገነዘበ፥ በአንድ ሀገራዊ ራዕይና ጥቅም ዙሪያ የተሰባሰበ ጠንካራ ኅብረት ገና ያልመሰረተ ፥ የተቃዋሚ ጎራ፥ በምርጫ ያሸነፈ ቢሆንም፥የመንግሥት ሥልጣን ለመረከብ ግን አስፈላጊውን ትግል በቆራጥነት ለማካሄድ ዝግጅቱም የሌለው ሆኗል፡፡

ሐ) የሕዝብ ተቃውሞ ያስደነገጠው፥ የሕዝቡ ቆጣና ትግል ያስበረገገው፥ ከሕዝብ የተነጠለ፥ የኅብረተሰብ ድጋፍ የሌለው፥ መሠረቱ የተናጋና ህጋዊነትም የሌለው ፀረ ህዝብ ሥርዓት አለ ፡፡ በሕዝብ ድምፅ የተሸነፈ መሆኑን ባለመቀበሉም፥ በሥልጣኑ ለመቆየት ሲል የሰላማዊ ዜጎችን ደም በግፍ እያፈሰሰ የሚገኝ አጥፊ ቡድን በሥልጣን ላይ አለ፡፡ ይህንን አስደንጋጭ ሁኔታ በመገንዘብ ፥ምዕራባውያኑ ፊታቸውን በመለስ ላይ በመጠኑም ቢሆን አዙረውበታል፡፡ መጋዣቸው ሆኖ ስለባጀ በቀላሉ ባይተዉትም የሕዝቡ ትግል እየገፋ ሲሄድ ግን እንደ ኢራኑ ሻህና እንደ ዛይሩ ሞቡቱ ሴሴ-ሴኮ እንደሚክዱት ጥርጥር አይኖርም፡፡

7. ዛሬ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ደረጃ፥ በዓለም ዙሪያ ተሰዶ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ/ት ዜጋ፥ በአንድ ላይ ተባብሮ ጠንካራ ትግል እያካሄደ ይገኛል፡፡ ከፊንላንድ እስከ ደቡብ አፍሪካ፥ ከኩዌት እስከ እስራኤል፥ ከካናዳ እስከ ዩናይትድ ስቴትስ ድረስ፥ ወገንን በሚያስገርምና በሚያኮራ የወያኔ መሪዎችን ደግሞ በሚያርበተብት አኳኋን፥ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት፥ የሻማ መብራት በማብራት፥ ሕዝባዊ ስብሰባ በማካሄድ፥ ገንዘብ በማሰባሰብ፥ በሚኖርበት ሀገር ላሉ መንግሥታት የተማፅኖ ደብዳቤ በማቅረብ በኩል ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ትግል በማካሄድ ላይ ነው፡፡

8. ኢትዮጵያውያን/ት ሀገር ወዳድ ምሁራንም የሚጠበቅባቸውን ብሔራዊ ግዴታ በመወጣት ላይ ናቸው። ለፓርላማ አባላት ለመንግሥታት መሪዎች፥ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ለልዩ ልዩ የትምህርትና ሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ተቋማት ደብዳቤ በመፃፍ የሚያደርጉት ተግባር ለትግሉ የሚሰጠው ዕመርታ የሚያኮራ ነው።_እዚህ ላይ በውጭ ሀገር ተወልደው ያደጉት ወጣቶች የሚያሳዩት ሀገራዊ ፍቅርና መቆርቆር ሳይጠቀስ የሚታለፍ ነጥብ አይሆንም።

ታዲያ ከላይ የተዘረዘሩት ሀቆች የተከሰቱት ባመዛኙ ፥ ከግንቦቱ ሕዝባዊ አመፅ ወዲህ መሆኑ አሌ የሚባል አይደለም። ይህን የሀገር ቤቱንና የዓለም አቀፉን ትግል አስተባብሮ ወያኔን መጣል ካልተቻል፥ ምን መደረግ እንደሚገባው ለመናገር ግራ የሚያጋባ ሆኗል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የሚጠይቀው ነገር ቢኖር፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች ተባብረው፥ የሕዝቡን ትግል በመምራት ወያኔን አስወግደው ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ መፍጠር እዲችሉ ነው። ከመለስዘ ስናዊ አገዛዝ ጋረ በወያኔ ፍርድ ቤት እሰጥ አገባ እንዲያካሂዱ ወይም በወያኔ ፓርላማ ወንበር እንዲያሞቁ ሆነ ዕርቀኑን የወጣ ከተማ አስተዳዳሪ ነን ብለው እንዲውገረገሩ አይፈልግም። ረሀብና በሽታ፥ ድኅነትና ጦርነት ፥ ያጠቃውን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት ሚቻለው፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች ጠንካራ ኅብረት ፈጥረው ሲታገሉ ብቻ ነው ብሎ የኢትዮጲያ ሕዝብ ያምናል። ይህንን ዕምነቱን ዕውን እንዲሆንለት ፈልጎም ይኸው በራሱ አነሳሽነት አይከፍሉ መስዋዕት በመክፈል ላይ ይገኛል። የሕዝቡን አመፅ አስባብሮ ኢትዮጵያን አሁን ከገባችበት ሁለንተናዊ አዘቅት ማውጣት፥የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ኃላፊነትና ተግባር ቢሆንም፥ በስሙ የተደራጁት የተቃዋሚ ድርጅቶች ግን የተለየ ኃላፊነት ግዴታና ተልዕኮ እንዳለበቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል። ይህን የሚፃረሩ ግን ራሳቸውን ከታቀዋሚ ወይም ከህዝብ የሚፈርጁ ሚናቸውን ዳግም መመርመር ይኖርባቸዋል።

ህብረት ህብረት የምንለው የአቋሞችን መለያያት በመርሳት ሳይሆን በዋናው ግብ ላይ ማተኮርና ክንድን ማስተባባር ወሳኝ መሆኑን በተመክሮ በማወቃችን ነው። ተባበሩ የምንለውም ሀቀኛ የህዝቡን ልጆች እንጂ ክህዝብ ማዕድ ቀርበው ወደ ወያኔ የሚውጡትን አስመሳዮች አይደለም። ዛሬ ሰልፉ ነጥሮ እየታየ ነው። ማን ከሕዝብ ማን ከአገዛዙ ጋር ተሰልፏል የሚለው በግልፅ እየታወቀ ነው። ስለዚህም የሕዝብ ድምፅ አይሰረቅም፤ ፀረ ህዝቡ አገዛዝ በሥልጣን አይቀጥልም፤ የህዝብ ትግልና አመፅ ወቅታዊም አቸናፊም ነው የሚሉ የኢትዮጵያ ሀቀኝ ልጆች ለታሪካዊው ፍልሚያ መተባባር አለባቸው። ሕዝብ ሌላ ጉንጭ አልፋና የአድርባዮች ቧልት መስማት አይፈልግም። ይህ ህገ ወጥ አገዛዝ የሚወገደው በትግል እንጂ በምለላ ወይም በራሱ ምርጫ ቦርድና ፍርድ ቤት ውሳኔ ከቶም ሊሆን አይችልምና የብሄራዊ ክብርና ሀገር አድን የህብረት ትግላችን ይፋፋም!!